# የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
# ALL ETHIOPIA UNITY PARTY

☎ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251-116-55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Abeba Ethiopia, Website:- www.kaeup.org e-mail: [illegible]@ethionet.et


ቁጥር
Ref. No. ____________
ቀን
Date ____________

## በመኢአድ ውስጥ በተወሰኑ ግለሰቦች የተፈጠረውን ችግር አስመልክቶ ከመኢአድ ጽ/ቤት የተሠጠ መግለጫ

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ኢትዮጵያ የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባት፣የህግ የበላይነትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፣ ረሃብ፣ በሽታ፣ ማይምነትና ድህነት የተወገዱባት፣ ሰላም፣ ፍትህ፣ እኩልነትና አንድነት የናኙባት አገር ትሆን ዘንድ በሰላማዊ መንገድ የሚታገል ህብረ ብሔራዊ ፓርቲ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ፓርቲያችን በሃያ ዓመቱ የትግል ጉዞው በርካታ የውጭና የውስጥ ፈተናዎች ሲገጥሙት ቆይተዋል፡፡ ሰሞኑን ያጋጠመው ችግርም ከእነዚህ ውስጥ የሚመደብ ነው፡፡ ከማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ውስጥ ለፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ያልተገዙ ጥቂት ግለሰቦች በቡድን ተደራጅተው ፓርቲውን ለማዳከም ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ተገኝተዋል፡፡ ይህ ቡድን በዋናነት እየተመራ ያለው በአቶ አሰፋ ሃብተወልድና በአቶ ማህተመ በኩረ መሆኑንም ከእንቅስቃሴዎቻቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡

የአፍራሹ ቡድን አባላት በየጊዜው የተለያዩ ሰንካላ ምክንያቶችን በመፍጠር በመኢአድ ውስጥ አለመረጋጋት እንዲስፋፋ ሙከራዎች ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ አንዳንዶቹም በመኢአድ ውስጥ እያሉ ከድርጅታቸው ጥቅም ይልቅ የሌሎች ፓርቲዎች ፍላጎትና ጥቅም እንዲከበር ለማድረግ የበኩላቸውን ጥረት አድርገዋል፡፡ ቀደም ሲልም በፓርቲው ውስጥ በበቀሉና ከሌላም ፓርቲ ሰርገው በገቡ እኩያን ድርጅቱ ሲታመስ መቆየቱና ጉዳዩ የማ/ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲያገኝ መደረጉ ይታወቃል፡፡ በዚህ ወቅትም እየተደረገ ያለው የመኢአድ አለመረጋጋት እንዲቀጥልና ፓርቲው ሁልጊዜም በውስጥ ችግሮች እየተተበተበ የተነሳለትንና የቆመለትን ዓላማ እንዳያሳካ የተዘጋጀለት ወጥመድ መሆኑን መገንዘብ አያስቸግርም፡፡ ፓርቲው ሙሉ ኃይሉን ተጠቅሞ የውስጥ ችግሮቹን ለመፍታት ጊዜ ሲሰጥ ከገዢው ፓርቲ ጋር የሚደረገው ትግል እንዲደበዝዝ ለማድረግ ከውጭና ከውስጥ እየተጠነሰሱበት ያሉ ደባዎች መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡

በአቶ አሰፋ ሃብተወልድና በአቶ ማህተመ በኩረ እየተመራ ያለው አፍራሽ ቡድን በየጊዜው ከመኢአድ ጽ/ቤት ውጭ በተለያዩ ቦታዎች ብዙውን ጊዜ በየመጠጥ ቤቶች በመሰብሰብ ፓርቲውን የሚበታትንበትን ዕቅድ ሲነድፍ ቆይቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቡድኑ መሪዎች መስከረም 18/2004 ዓ.ም አቶ ፀጋዬ ግዛውን፣ አቶ ጌታቸው ባያፈርስን፣ ዶ/ር በዛብህ ደምሴን፣ አቶ አቤል ሙሴንና (ሻምበል ግዛው ተሰማን ስብሰባው ሊጠናቀቅ ሲል የደረሱ ናቸው) በፓርቲው ጽ/ቤት አሳቻ ክፍል በመሰብሰብ ህገ ወጥ ውሳኔዎችን አስተላልፈዋል፡፡ ይህንንም በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን፣ በውጭ ሃገር ለሚገኙ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶችና ለሌሎችም ረጭተዋል፤ ውሳኔዎቻቸውም፥

+251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251-116-55 12 56 Fax +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa Ethiopia, Website:- www.kaeup.org e-mail: [illegible]@ethionet.et

ቁጥር
Ref. No.
ቀን
Date

1ኛ. የመኢአድ ፕሬዚዳንት ሃላፊነታቸውን አልተወጡም በሚል ጉዳያቸው ለህግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ ቀርቦ ኮሚቴው በአጭር ጊዜ እንዲያጣራ እና የማጣራት ሪፖርቱንም ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዲያቀርብ፣(ርክክብ እንዲደረግ እና ሥራ እንዲጀመር ባልተደረገበት እንዲሁም ቋሚ ኮሚቴ ባልተቋቋመበት)

2ኛ. የፓርቲው ዋና ጸሃፊ አጥፍተዋል የተባሉባቸው ጉዳዮች ለህግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ እንዲቀርቡና ሁኔታው የውሳኔ ሃሳብ እንዲሰጥበት፣ እስከዚያ ድረስ ዋና ጸሃፊው ከፓርቲው ጸሃፊነትና አባልነት ታግደው እንዲቆዩ፣

3ኛ. ከላይ የቀረቡት ችግሮች ያሏቸው ሁለቱ ነጥቦች የመጨረሻ ውሳኔ የሚያገኙት በማዕከላዊ ምክር ቤቱ በመሆኑ የማዕከላዊ ምክር ቤቱ በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ እንዲጠራ እና

4ኛ. ለፓርቲው ደህንነት ሲባል የድርጅቱ ማህተም በአቶ ማህተመ በኩረ እጅ እንዲቆይ የሚሉ ናቸው።

የአፍራሽ ቡድኑ በዕለቱ ያካሄደው ስብሰባ ገና ከጅምሩ ህገ ወጥ ነበር፤ ይኸውም፥

1. በመኢአድ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 15.2.1. መሠረት አንድ ስብሰባ የሚጀመረው ምልአተ ጉባዔው ሲሟላ ማለትም ከጠቅላላ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላቱ ቁጥር ግማሽ ሲደመር አንድ ወይም 50%+1 ሲሆን ነው። ነገር ግን በዕለቱ የተገኙት አባላት ቁጥር ስድስት (6) ብቻ ሲሆን ሰባተኛው ተሰብሳቢ ስብሰባው ሊጠናቀቅ ሲል የመጡ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ የመኢአድ ሥራ አስፈጻሚ ቁጥር በጠቅላላ አስራ ስምንት (18) ሲሆን ስብሰባውን ለመጀመር ቢያንስ አስር (10) አባላት መገኘት ነበረባቸው። ነገር ግን ወንጀል በመፈጸም ኮረም እንደሞላ ለማስመሰል ጥረት አድርገዋል። ይኸውም፥

   1.1በወቅቱ አዲስ አበባ ውስጥ የሌሉና ሰሜን ወሎ ኗሪ የሆኑት አቶ በለጠ ገብሬ በስብሰባው ላይ ተገኝተው እንደፈረሙ አስመስለው ስማቸውንና የሃሰት ፊርማ አስፍረዋል።

   1.2 በስብሰባው ላይ ያልተገኙ ሁለት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን- ለአንደኛዋ የቃለ ጉባዔውን ይዘት ሳይገልጹ በቅንነት የቀረቡ መስለው ፓርቲውን ለማዳን ነው ቶሎ ፈርሙ በማለት በአደባባይ ያስፈረሙ ሲሆን ሌላውን ደግሞ በድምጽ ብልጫ ስለበለጥናቸሁ ፈርሙ በማለት እንዳስፈረሟቸው ታውቋል።

1.3 በዕለቱ አካሂያድን ባሉት ስብሰባ ላይ ከተገኙት ውስጥ፥

- አቶ ጌታቸው ባያፈርስ አንዱ ናቸው። እኝህ ሰው በራሳቸው ፈቃድ የመልቀቂያ ደብዳቤ አቅርበው ከመኢአድ የለቀቁና አንድነት ለፍትህና

☎ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251-116-55 12 56 Fax +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Abeba Ethiopia, Website:- www.kaeup.org e-mail:-

ቁጥር፡
Ref. No.
ቀን
Date

ለዲሞክራሲ ፓርቲ ውስጥ በመግባት የአባልነትና የወርሃዊ መዋጮ ክፍያ መፈጸማቸው ተረጋግጧል፡፡ እነዚህን ምክንያቶች መሠረት በማድረግ እኛም ጉዳዩን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያሳወቅን በመሆኑና ያቀረቡት የመልቀቂያ ደብዳቤም ተቀባይነት ማግኘቱን በመግለጽ ምላሽ የሰጠናቸው በመሆኑ የመኢአድ አባል አይደሉም፡፡

- ሌላው አቶ አሰፋ ሃብተወልድ ሲሆኑ እራሳቸው በጻፉት የመልቀቂያ ደብዳቤ ከመኢአድ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት የለቀቁና በቦታቸውም ሌላ ሰው እንዲተካ የጠየቁና ጥያቄያቸውም ተቀባይነት አግኝቶ በደብዳቤ ምላሽ የተሰጣቸው በመሆኑ የመኢአድ ሥራ አስፈፃሚ አባል አይደሉም፡፡

- ሌላው አቶ ማህተመ በኩረ ሲሆኑ የፓርቲውን ማህተምና የፕሬዝዳንቱን ቲተር ከጽ/ቤታችን ውጭ በመሰወርና ለድርጅቱ አገልግሎት እንዳይውል በማድረግ የፓርቲውን እንቅስቃሴ በከፍተኛ ደረጃ እንዲስተጓጎል አድርገዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በማዕከላዊ ኮሚቴ ለተመረጡት ለአዲሱ የአስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ የፓርቲውን ማህተም እንዲያስረክቡ በተደጋጋሚ ቢጠየቁም ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በማሳወቃቸው ከመስከረም 15/2004 ዓ.ም ጀምሮ ከፓርቲው የታገዱ ናቸው፡፡

ከተራ ቁጥር 1.1 እስከ 1.3 ድረስ የተዘረዘሩት ነጥቦች በዕለቱ ተካሄደ ባሉት ስብሰባ ሙሉ በሙሉ የተካፈሉት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ሦስት (3) ብቻ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ስለዚህ ስብሰባው ኮረም ያልሞላ ስለ ነበረ ተቀባይነት የለውም፡፡

2. ተካሄደ ባሉት ስብሰባ የፓርቲው ፕሬዚዳንት ወይም ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንትና ዋና ጸሃፊው ያልተገኙ በመሆኑ ህገ ወጥ ነው፡፡

3. ፕሬዚዳንቱም ሆኑ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንቱ በሃገር ውስጥ እያሉ ምክትል ፕሬዚዳንቱ አባል ቢሆኑ ኖሮም መሰብሰብ አይችሉም በዚህም ስብሰባው ህገ ወጥ ነው፡፡

በተዘረዘሩት ምክንያቶች ተካሄደ የተባለው ስብሰባ ፍጹም ህገ ወጥ መሆኑን የመኢአድ አባላትና ደጋፊዎች እንዲረዱልን እንፈልጋለን፡፡

ህገ ወጡ ቡድን ባዘጋጀው ቃለ ጉባዔና ከቡድኑ አስተባባሪዎች አንዱ የሆኑት ከመገናኛ ብዙሃን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ፕሬዚዳንቱ ጠቅላላ ጉባዔ የሰጣቸውን ኃላፊነት አልተወጡም ካሉ በኋላ ምክንያቶቹንም እንደሚከተለው ይጠቅሳሉ፡፡ ‹‹የሥራ አስፈፃሚው ሳምንታዊ ስብሰባ ከአንድ ወር ላላነሰ ጊዜ እንዳይካሄድ አድርገዋል›› ይላሉ፡፡ ነገር ግን ይኸ አባባል ከእውነት የራቀ ነው፡፡ ምክንያቱም ከሃምሌ 30/2003 ዓመተ

+251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251-116-55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Abeba Ethiopia, Website: www.kaeup.org e-mail: ... ethionet.et

ቁጥር
Ref. No. ____________
ቀን
Date ____________

ምህረቱ የማዕከላዊ ምክር ቤት ስብሰባ በኋላ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ለስድስት ጊዜ ያህል ተሰብስቧልና።

ሌላው የፕሬዚዳንቱ ጥፋት ያሉት ‹‹የፋይናንስ ገቢና ወጭ ባግባቡ እንዲታወቅ አለማድረጋቸው፣ የገቢና የወጭ መዝገብ አለመኖርና የሦስት ዓመት ገቢና ወጭ እንዲታወቅ አለማድረጋቸው ነው።›› ይላሉ።

ነገር ግን እነዚህ የተዘረዘሩት ጉዳዮች የፕሬዚዳንቱ ኃላፊነት ሳይሆኑ የአስተዳደርና ፋይናንስ መሆናቸውን የመኢአድ መተዳደሪያ ደንብ በግልጽ አስቀምጧል። ለምሳሌ፥ አንቀጽ 16.10.2. የአስተዳደርና የፋይናንስ ኃላፊውን የሥራ ድርሻ ሲገልጽ ‹‹የፓርቲው ገንዘብና ንብረት በትክክል ተጠብቆ በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ የሂሳብ አያያዝና የንብረት አጠባበቅን ያጠናክራል›› ይላል። በአንቀጽ 16.10.4. ላይም ‹‹ልዩ ልዩ የሂሳብ ሰነዶችን በማዘጋጀት የፓርቲው ሂሳብ አያያዝ በህግ ተቀባይነት ያለው የሂሳብ አሠራር ሥልትን የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል።" ሲል በአንቀጽ 16.10.6. ደግሞ" በየወቅቱ አስፈላጊ የሂሳብ መግለጫዎችን በማዘጋጀት እንደሁኔታው ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው፣ ለማዕከላዊ ም/ቤቱ ወይም ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል።" ይላል። ከመስከረም 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሐምሌ 30/2003 ዓ.ም. ድረስ የአስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ ሆነው ያገለገሉት እራሳቸው አቶ ማህተመ በኩረ በመሆናቸው ጉዳዩ የሚመለከተው እሳቸውን መሆኑን ደግመን ማስገንዘብ ተገደናል።

ሌላው በፕሬዚዳንቱ ላይ የቀረበው ክስ የሦስት ዓመት ገቢና ወጭ እንዲታወቅ አለማድረጋቸው የሚለው ነው። ፓርቲው 36,000.00 ብር በመክፈል ሂሳቡን ሠርቶ የሚዘጋ ባለሙያ ቀጥሮ ነበር፤ ነገር ግን በወቅቱ በፓርቲው ላይ ችግር ሲፈጥሩ የነበሩትና በማዕከላዊው ኮሚቴ ውሳኔ ከፓርቲው ከተወገዱ ሰዎች ወስጥ የሂሳቡ ጉዳይ የሚመለከታቸው ሦስት ሰዎች ለማስመርመር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ሥራው መከናወን አልቻለም። ጉዳዩም በፍርድ ቤት የተያዘ በመሆኑ ሂሳብ ክፍል፣ ንብረት ክፍልና መዝገብ ቤቶችን እስካሁን እንደተዘጉ ነው ያሉት።

በፕሬዚዳንቱ ላይ የቀረበው ሌላው ክስ "በውጭ ከሚገኙ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት እንዲቋረጥ አድርገዋል" የተሰኘ ነው። ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኙ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶችን በተመለከተ የውጭ ጉዳይ ኃላፊው የሥራ ድርሻ መሆኑ በመተዳደሪያ ደንባችን በአንቀጽ 16.7 በማያሻማ አገላለጽ ተቀምጧል። በወቅቱ ተከስቶ የነበረውን ችግር የፈጠሩት በጊዜው የውጭ ጉዳይ ኃላፊ የነበሩት አቶ ያዕቆብ ልኬ መሆናቸው በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ግንዛቤ ላይ የተደረሰ መሆኑ ይታወሳል። እንዲያውም ፕሬዚዳንቱ የሻከረው ግንኙነት እንዲለሰልስ ብዙ ጥረት አድርገው ውጤትም በመታየት ላይ ይገኛል። ነገር ግን ፕሬዚዳንቱ መኢአድ ከሚከተለው የትግል ስልት ካፈነገጡ

☎ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251-116-55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Abeba Ethiopia, Website:- www.kaeup.org e-mail: [illegible]@ethionet.et


ቁጥር:
Ref. No. ______
ቀን
Date ______

ሰዎችና በውጭ ሆነው አመራር እንስጥ ከሚሉ ጋር ግንኙነት እንዲቋረጥ አድርገዋል፤ ይህ ደግሞ የሚያስመሰግናቸው እንጂ የሚያስወቅሳቸው ተግባር አይደለም።

ህገ ወጡ ቡድን አሳለፍኩ ያለው ሌላ ውሳኔ የፓርቲውን ዋና ጸሃፊ አግጃለሁ ማለቱ ነው። ለዚህም ካቀረባቸው ምክንያቶች አንዱ ለህግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ ቃላቸውን ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የሚል ነው።

መስከረም 6/2004 ዓ.ም ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ባካሄደው ስብሰባ ላይ የተወሰኑ አባላት በአቶ ተስፋዬ ታሪኩ ላይ ቅሬታ በማቅረባቸውና እሳቸውም በወቅቱ በስብሰባው ለይ ባለመኖራቸው ምላሻቸውን ወዲያው መስማት አልተቻለም። ይህ በመሆኑም ሦስት አባላት ያሉት አጣሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ ችግሮችን እንዲያጣራና የማጣራት ውጤቱን ሪፖርትም ለሥራ አስፈጻሚው እንዲያቀርብ ተወሰነ። አጣሪ ኮሚቴው ሥራውን እንደጀመረ አቶ ተስፋዬ ታሪኩ ለኮሚቴው የቀረቡብኝ ቅሬታዎች በቃል ሳይሆን በጽሁፍ ይሰጠኝ አሉ። ይህ የሚያሳየው ደግሞ እነሱ እንዳሉት ቃላቸውን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ሳይሆን የመኢአድ መተዳደሪያ ደንብ የሰጣቸውን መብት ተጠቅመው ክሱ በጽሁፍ ይድረሰኝ ማለታቸውን ነው። በመሆኑም መብታቸው እንዲከበር በመጠየቃቸው ብቻ ማጣራቱ ሳይካሄድና ውሳኔ ላይ ሳይደረስ ጥፋተኛ ናቸው ማለት ከስህተት ላይ መውደቅ ነው። ደንቡን ስናይም

አንቀጽ 20.5. "የክሱ አቀራረብ በጽሁፍ ይሆናል"
20.5.1. "የጥፋቱን ዓይነት በዝርዝር የያዘ ይሆናል"
20.5.3. "ለተከሳሹ ክሱ በጽሁፍ እንዲደርሰው ይደረጋል" ይላል።

ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የአቶ ተስፋዬ ጉዳይ እንዲጣራ የወሰነው በዕለቱ በተቋቋመው ጊዜያዊ ኮሚቴ እንጂ በህግና ሥነ-ሥርዓት ኮሚቴ አይደለም።

የአፍራሽ ቡድኑ አባላት ከፈጸሟቸው ህገ ወጥ ተግባራት ሌላኛው መስከረም 14/2004 ዓ.ም ነባሩን የአዲስ አበባ የመኢአድ ምክር ቤትና ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴን አፍርሰው ከዲሞክራሲያዊ ምርጫ ውጭ በሆነ መንገድ በራሳቸው አምሳል የተቀረጸ ምክር ቤትና ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ማቋቋመ መሞከራቸው ነው።

ህገ ወጡ ቡድን በዕለቱ ያከናወነው የምክር ቤትና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምስረታ ስህተቶች የተንፀባረቁበት ነው፤ እነዚህም፥

1. በዕለቱ የተፈጸመውን የምክር ቤትና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምስረታ የማዕከላዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የማያውቀውና የምርጫ ሂደቱንም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተወካይ በይፋ ልኮ ያላስፈጸመው በመሆኑ፣

☎ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251-116-55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa Ethiopia, Website:- www.kaeup.org e-mail: [illegible]@ethionet.et

ቁጥር
Ref. No. ________
ቀን
Date ________

2. በዕለቱ የተደረገውን ምርጫ የአዲስ አበባ መኢአድን በበላይነት የሚመሩት የማዕከላዊ ቀጠና ኃላፊው ያልተስማሙበት በመሆኑ፣
3. በወቅቱ የተካሄደው የምርጫ ሂደትም ማጭበርበር የተፈጸመበትና ኢ-ዲሞክራሲያዊ ነበር። ይኸውም የአፍራሽ ቡድኑ አባላት የሆኑት እና አቶ ፀጋዬ ግዛው፣ የሌላ ፓርቲ አባል የሆኑት አቶ ጌታቸው ባያፈርስና ሌሎቹም ቀድመው የተዘጋጁትን ድራማ የተወኑበት መድረክ ነበር።
4. እነሱ ከሚፈልጓቸው በስተቀር አብዛኛዎቹ አባላት በሥፍራው እንዲገኙ በቂ ጥሪ ያልተደረገበትና ምርጫውም አስፈላጊ ዝግጅት ያልተካሄደበት በመሆኑ ተቀባይነት የለውም። ድርጊቱም የአፍራሽ ቡድኑ አባላት የቱን ያህል እራሳቸውን ከህግ በላይ ማድረጋቸውን የሚያሳይ ነው።

ሁኔታው ያሳዘናቸው የአዲስ አበባ የመኢአድ አባላት ድርጊቱን ተቃውመው ለማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አቤቱታ ለማቅረብ ፔትሽን እየፈረሙ መሆኑ ታውቋል። የህገ ወጡ ቡድን ሌላው ደባ ባለፉት ጊዜያት ፓርቲያችንን በመጉዳታቸው በዚሁ ቡድን ጥያቄ እና ውሳኔ ጭምር ከተሰናበቱ ግለሰቦች ጋር ግንኙነት በመመሥረት የኢሜል መልዕክቶችን በእነሱ በኩል እንዲተላለፉ ማድረጉና ከሌሎቹም ጋር እንደዚሁ እየተገናኘ መመሳጠሩ ነው።

መላው የፓርቲያችን አባላት! በየጊዜው እየገጠሙን ያሉት የውስጥና የውጭ ችግሮች ተስፋ ሳያስቆርጧችሁ ዛሬም እንደ ትናንቱ ለኢትዮጵያ ህዝብ መብት መከበር እንደምትታገሉ እምነታችን የጸና ነው። ከስንዴ መሃል እንክርዳድ አይጠፋምና እንክርዳዱን እያረምንና ፍሬውንም ከገለባው እየለየን ትግላችንን ወደፊት እንደምንቀጥል ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ አይገባንም። የፓርቲውን ማህተም በተመለከተም ህገወጥ ተግባር እንዳይፈፀምበት ጉዳዩን ለፖሊስና ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አሳውቀን ሁኔታውን በህግ እየተከታተልን ነው።

የተከበራችሁ ደጋፊዎቻችን! መኢአድ ጠንካራ የሕዝብ ወገን በመሆኑ ዛሬ ብቻ ሳይሆን መሠሪዎች ለወደፊትም ቢሆን ትግላችንን ለማዳከም መሞከራቸው አይቀርም። ፀረ-ዲሞክራሲ እና ፀረ-ሕዝብ ኃይሎች እስካሉ ድረስ ትግላችን የሚገረሩ አይጠፉምና በተለያዩ ጊዜያት በተፈጠሩብን የውስጥ ችግሮች መሰላቸት ሳታደርጉ አሁንም እንደ ወትሮአችሁ ከጎናችን በመቆም ድጋፋችሁን እንድትሰጡን የአክብሮት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

የመኢአድ ተልዕኮ በሃቀኛና በጠንካራ አባላቱ ይሳካል!!!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

ኢ/ር ኃይሉ ሻውል
የመኢአድ ፕሬዝዳንት

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/
መስከረም 25 ቀን 2004 ዓ.ም